በስመአብ ወወልድ

(የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ነው ለኛ ለሚድኑ ግን የእግዚአብሔር ቃይል ነውና። 1 ኛ.ቆሮ 1-18)

ዘክረ መስቀል

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ሞቶ ተቀብሮ በሥልጣኑ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሳ በኋላ ድውያን መስቀሉን እየዳሰሱ መፈወስ፣ ህሙማንም በመስቀሉ እየታሹ መዳን ጀመሩ። ይህንን ያዩ ክርስቶስን ጠልተው የገደሉ አይሁዶች በመስቀል የሚታየውን፤ የሚሰራውን ድንቅ ድንቅ ተዓምር ተመልክተው ይህን ያዩ ሁሉ በእርሱ ያምናሉ ብለው የጌታችንን መስቀል እንዲቀበርና ደብዛው እንዲጠፋ ለ 300 ዓመታት ያህል በክርስምድር ቆሻሻ መጣያ ቦታ የጌታችንን መስቀል ጥለው የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሁሉ ጉድፍ እንዲጥሉበት አደረጉ ማንኛውም ቤተሰብ የቤቱን ጥራጊ እያወጣ በመስቀሉ ላይ እንዲቆልል ተደርጎ ጥራጊ ሲጣልበት በመኖሩ ቦታው ኮረብታማ ሆኖ ነበር። በጊዜው የነበሩ ክርስቲያኖች ምንም እንኳን መስቀሉን በድፍረት ሄደው ማውጣት ባይችሉም ስለመስቀሉ ክብርና እና ስለተቀበረበት ቦታ ያውቁ ነበር። ከጊዜያት በኋላ በሮማ ጀነራሎች በአስባስያኖስ በጥጦስ ወረራ በ 70 ዓ.ም ክርስቲያኖች ኢየሩሳሌምን ለቀው ስለወጡ መስቀሉ የተቀበሩበት ቦታ ወዴት እንደሆነ ለማወቅ አልተቻለም።

የንግስት እሌኒ ልጅ የሆነው ንጉስ ቆስጠንጢኖስም ለ 300 ዓመት በስደት፤ በመከራ የኖረች ቤተክርስቲያንን እረፍት ሊሠጥ እንዲሁም ለ 40 ዓመታት ያህል ለአራት ተከፍላ ትገዛ የነበረችውን ሮም አንድ ሊያደርግ ታላቅ ጦርነትን ከጠላቱ ከመክስምያኖስ ጋር ባደረገ ጊዜ እግዚአብሔር በአንድ ሌሊት ‹‹በዚህ ምልክት ጠላትህን ድል ታደርጋለህ›› ብሎ የመስቀልን ቅርጽ በራዕይ አሳየው በዚህም ጊዜ ንጉሱ በራዕይ ያየውን የመስቀል ቅርጽ በወታደሮቹ የጦር ልብስ፣ ጋሻ አንዲሁም በየፈረሳቸው ኮርቻ ላይ ሁሉ ሳይቀር አስቀረጸ ለጦርነቱም ሲወጣ እናቱ ድል ካደረገ የጌታችንን መስቀል ፈልጋ እንደምታገኝ ስለትን ተሳለች። በጦርነቱም ንጉሱ ቆስጠንጢኖስ ድል አደረገ እናቱ ቅድስት እሌኒም የጌታችንን መስቀል ከተቀበረበት ለማውጣት ወደ ኢየሩሳሌም በ 321 ዓ.ም ጉዞን ጀመረች ልጇም ብዙ ወታደሮችን፣ እንዲሁም ለመስቀሉ ፍለጋ የሚያስፈልጋትን ነገሮች በሙሉ አዘጋጅቶ ሸኛት።

ንግስት እሌኒም ኢየሩሳሌም ከገባች በኋላ ኮረብታ ቦታዎችን እያስቆፈረች መስቀሉን ብትፈልግም ልታገኘው አልቻለችም። የአይሁድን ህዝብ በሙሉ የጎልጎታን ኮረብታዎች እንዲጠርጉ አዘዘች ሆኖም መስቀሉን ልታገኘው አልቻለችም በዚህም አዝና የፈጣሪ ፈቃድ መሆኑን ላረጋግጥ ብላ ሱባኤ ገባች ሱባኤዋንም እንደጨረሰች የአይሁድ ሽማግሌዎችን መጠየቅ ጀመረች ሆኖም እነርሱ ፈቃደኞች ስላልነበሩ አሰረቻቸው ነገር እነርሱ ባለመናገራቸው ጸኑ። ከብዙ ድካምና ፍለጋ በኋላም አንድ ኪራኮስ የተባለ አረጋዊ ‹‹አባቶቻችን እንደነገሩን ከሆነ ከእነዚህ ኮረብታዎች በአንዱ ነው በየትኛው እንደሆነ ግን አላውቀውም›› በማለት ከኢየሩሳሌም ወጣብለው የሚገኙትን ትልልቅ ኮረብታዎች አሳያት።

ኮረብታዎቹ እጅግ ትልልቅ ስለነበሩ የትኛው እንደሆነ ለማወቅ ተቸገረች በመጨረሻም ደመራን አስደምራ መስከረም 16 ቀን አስለኮሠችው ደመራውም ላይ ብዙ እጣንን አስደረገችበት የደመራው ጢስም ወደ ላይ ወጥቶ መስቀሉ ካለበት ኮረብታ ላይ እንደቀስተደመና አመለከተ። ንግስት እሌኒም መስቀሉ ያለበትን ቦታ አውቃ ቁፋሮውን አስጀመረች ከብዙ ድካምና ረጅም ቁፋሮ በኋላ በእግዚአብሔር ቸርነት መጋቢት 10 ቀን ከተቀበረበት ወጣ። ንግስት እሌኒም በጎልጎታ ቤተክርስቲያንን አሳንፃ መስቀሉን አኖረችው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ዲ/ን ታሪኩ ታደሰ

13/01/2009

መስቀል ኃይልነ መስቀል ኃይላችን ነው ኃይላችን መስቀል ነው

መስቀል ፅንነ የሚያጸናን መስቀል ነው

መስቀል ቤዛነ መስቀል ቤዛችን ነው

መስቀል መድኃኒተ ኑብስነ መስቀል የኑብሳችን መዳኛ ነው

ለመስቀል ትርኢት ትረካ የተዘጋጀ።